በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት
ፍትህ ቢሮ
የሕግ ምክር፣ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት

THE AMAHARA NATIONAL REGIONAL STATE
JUSTICE BUREAU
LEGAL COUNSELING, DRAFTING AND COMPILATION
DIRECTORATE

ቁጥር የሕ/ም/ማጠ/ዳ/..5465/58..
ቀን 21/12/2018 ዓ.ም

ለአብክመ ገቢዎች ቢሮ
ባህር ዳር፤

ጉዳዩ፡- የመመሪያ ምዝገባን ይመለከታል

የአማራ ክልል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 292/2017 (ሀምሌ 2018 ዓ.ም የተሻሻለ) ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም አዋጁ ከመዉጣቱ በፊት በሥራ ላይ የነበረ መመሪያን ለፍትህ ቢሮው በመላክ ማስመዝገብ እንዳለበት ደንግጓል፡፡

በዚህ መሰረት ገቢዎች ቢሮ በቁጥር ገዎችም.ቢ/3.8/265 በቀን 27/11/2018 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ "የታክስ አስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ መመሪያ ቁጥር አገቢ 27/2017" እንዲመዘገብ መላኩ ይታወሳል፡፡

ስለሆነም ፍትህ ቢሮ በአዋጁ አንቀጽ 16 መሠረት የተላከለትን መመሪያ ሕጋዊነቱን፣ መሰረታዊ መብቶችና መርሆችን የማይጥስ መሆኑን መርምሮ መመሪያው በክልል ደረጃ ቁጥር ተሰጥቶ መመሪያ ቁጥር 157/2018 ዓ.ም ሆኖ ስራ ላይ እንዲዉል የመዘገበው ስለሆነ የተመዘገበውን መመሪያ በተቋማችሁ ድረ ገጽ ጭናችሁ ተግባራዊ ማድረግ የምትችሉ መሆኑን እየገለጽን የተመዘገበዉን መመሪያ ቅጅ 10 ገጽ በሀርድና ሶፍት ኮፒ በዚህ ሸኚ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

'ከሰላምታ ጋር'

ሺድጋፍ ኃይሌ
የሕግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠቃለል
ዳይሬክቶሬት የክልል ዐቃቤ ሕግ

ግልባጭ//

- ለቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት፤ (ያለ አባሪ)
- ለፍት/ሕግ ጉዳ/ዘር/ምክትል ቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት
  ፍትሕ ቢሮ

ቀር



የአብክመ ገቢዎች ቢሮ
ANRS Bureau of Revenue

ስለምናገለግልዎ ደስታ ይሰማናል - Serve with Passion

የታክስ አስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ መመሪያ

ቁጥር አገቢ 157/2018



ጥቅምት /2017 ዓ.ም

ባህር ዳር

መመሪያ ቁጥር 157/2018

የታክስ አስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ መመሪያ

ገቢዎች ቢሮ የቅጣት ይነሳልኝ ማመልከቻ ከግብር ከፋዮች ሲቀርብለት ወይም በራሱ ተነሳሽነት በታክስ ከፋይ ላይ የተጣለን አስተዳደራዊ ቅጣት በሙሉ ወይም በከፊል ሊያነሳ እንደሚችል በክልሉ ታክስ አስተዳደር አዋጅ የተደነገገ በመሆኑ፤

አስተዳደራዊ ቅጣት ሙለ በሙሉ ወይም በከፊል ማንሳት ታክስ ከፋዮች ውዝፍ ፍሬ ታክስ ሳይዘገይ ለመሰብሰብ የሚያስችል መሆኑ ስለታመነበት እና ቅጣቱ በሙሉ ወይም በከፊል መነሳት የአስተዳደራዊ ቅጣት አላማን በጠበቀ ሁኔታ እንዲፈጸም ለማድረግ የቅጣት ደረጃ ምደባዎችን ማሻሻል አስፈሊጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ቀድሞ ሥራ ላይ በነበረ የቅጣት አነሳስ መመሪያ ያልተሸፈኑ አስተዳደራዊ ቅጣቶች እንዲካተቱ ማድረግ፣ የቅጣት አነሳስ ሁኔታው ፍትሃዊ እንዲሆን ማድረግ እና ቅጣቱን ስለሚያነሳ የሥራ ክፍል በይበልጥ ግልጽ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በዚህ መሠረት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ቢሮ በክልሉ ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 114 ንዑስ አንቀጽ 4 ላይ በተሠጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል::

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "**የታክስ አስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ መመሪያ ቁጥር 157/2018**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

2. ትርጓሜ

ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር :-

1) "**የታክስ ህግ** " ማለት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 36 የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል::
2) "**አስተዳደራዊ ቅጣት**" ማለት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የታክስ አስተዳደር አዋጅ 241/2008 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 24 የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል::
3) "**የታክስ ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል**" ማለት በክልሉ ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በቢሮው፣ በመምሪያ፣ በከተማ፣ በወረዳ እና በክፍለ ከተማ የተቋቋመ የደንበኞች አገልግሎት ዋና የሥራ ሂደት ወይም የግብር ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የግብር አወሳሰንና አሰባሰብ

ከትትል የሥራ ሂደት በአስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ ላይ በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ሲቀርብ በማጣራት ለቢሮ ኃላፊ ወይም ለሚወክለው የስራ ኃላፊ ወይም ለመምሪያ ኃላፊ ወይም ለጽ/ቤት ኃላፊ የውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብ የሥራ ክፍል ነው::

4) **"ሐራጅ/ጨረታ"** ማለት የታክስ ዕዳን ባለመክፈል በገቢዎች ቢሮ የተያዘን ንብረት በግልጽ ጨረታ ሥነ-ሥርዓት የመሸጥ ሂደት ነው::

5) **"ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት"** ማለት በተወሰነ አካባቢ በተከሰተ የተፈጥሮ ወይም በሰዉ ሰራሽ ማለትም ጦርነት፣ ዝርፊያ፣ ጎርፍ ፣ ቃጠሎ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ መብረቅ፣ ተምች ፣ ወይም ሌላ ተመሳሳይ ክስተት ሲያጋጥም ሲሆን ጽኑ ህመም ወይም ሞት በድርጅቱ ወኪሎችና እንደራሴዎች የደረሰ ጽኑ ህመም ወይም ሞትን ይጨምራል::

6) **"ጽኑ ህመም"** ማለት ታክስ ከፋዩ የውሳኔ ማስታወቂያ ከደረሰው ወይም አስታውቆ መክፈል ባለበት ጊዜ ውስጥ ተንቀሳቅሶ መስራት የማያስችል ህመም ላይ ስለመሆኑ የህክምና ተቋም በህክምና ማስረጃ የተረጋገጥ ሆኖ በጊዜው የንግድ ስራ እንቅስቃሴውን የሚመራለት የታክስ እንደራሴ የሌለው ሲሆን ነው::

7) **"የቅጣት ደረጃ ምደባ "** ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት በከፊል የሚነሳ አስተዳደራዊ ቅጣት ለመወሰን ሲባል በታክስ ህጎች የተዘረዘሩትን አስተዳደራዊ ቅጣቶች ዝቅተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ ደረጃ በማለት የተደለደለበት የቅጣት ምደባ ደረጃ ነው::

8) **"ገቢዎች ቢሮ "** ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ቢሮ ማለት ሲሆን በየደረጃው የሚገኙ የገቢ ተቋማትንም ይጨምራል::

9) **"ኃላፊ"** ማለት የገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ወይም እሱ የሚወክለው የሥራ ኃላፊ ወይም በየደረጃው የሚገኝ የመምሪያ ወይም የጽ/ቤት ኃላፊ ነው::

10) **"አዋጅ"** ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 ነው::

11) በዚህ መመሪያ ውስጥ ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላትና ሀረጎች በክልሉ ገቢ ግብር አዋጅ እና በታክስ አስተዳደር አዋጅ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ::

3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ታክስ አስተዳደር አዋጅ፣ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ እና በቴምብር ቀረጥ አዋጅ መሠረት በተጣለ የታክስ አስተዳደራዊ ቅጣት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል::

ክፍል ሁለት

አስተዳደራዊ ቅጣት የሚነሳበትና የማይነሳበት ሁኔታ እና መጣኔ

4. አስተዳደራዊ ቅጣት የሚነሳበት ሁኔታ

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 እና 13 ድንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆኖ በታክስ ህግ የተጣሉ አስተዳደራዊ ቅጣቶች ከዚህ በታች በአንቀጽ 7 እና 8 በተደነገገው መሰረት በከፊል ወይም በሙሉ ሊነሱ ይችላሉ::

ተ.ቁ	ፍሬ ታክስ፤ ወለድ እና የማይነሳው ቅጣት የተከፈለበት ጊዜ	የሚነሳው ቅጣት መጣኔ በቅጣት ደረጃ ምደባ መሠረት		
		በዝቅተኛ ደረጃ የሚመደብ ቅጣት	በመካከለኛ ደረጃ የሚመደብ ቅጣት	በከፍተኛ ደረጃ የሚመደብ ቅጣት
1	ታክስ ከፋዩ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ወይም በቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል ወይም በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም በፍ/ቤት ውሳኔ መሠረት የተሰጠ የታክስ ማስታወቂያ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ቀርቦ፡-			
1.1	በአንድ ጊዜ አጠቃሎ ከከፈለ	90	80	70
1.2	ቢሮው በሚሰጠው እስከ 6 ወራት በሚደርስ የክፍያ ስምምነት ጊዜ ከከፈለ	80	70	60
1.3	ቢሮው በሚሰጠው ከ6 ወራት በላይ በሆነ የክፍያ ስምምነት ጊዜ ከከፈለ	70	60	50
2	ታክስ ከፋዩ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ወይም በቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል ወይም በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም በፍ/ቤት ውሳኔ መሠረት የተሰጠ የታክስ ማስታወቂያ በደረሰው ከ31 እስከ 60 ቀናት ውስጥ ባለው ጊዜ ቀርቦ፡-			
2.1	በአንድ ጊዜ አጠቃሎ ከከፈለ	80	70	60
2.2	ቢሮው በሚሰጠው እስከ 6 ወራት በሚደርስ የክፍያ ስምምነት ጊዜ ከከፈለ	70	60	50
2.3	ቢሮው በሚሰጠው ከ6 ወራት በላይ በሆነ የክፍያ ስምምነት ጊዜ ከከፈለ	60	50	40
3	ታክስ ከፋዩ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ወይም በቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል ወይም በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም በፍ/ቤት ውሳኔ መሠረት የተሰጠ የታክስ ማስታወቂያ ደርሶት የሚፈለግበትን ታክስ ሳይከፍል 60 ቀን ያለፈው ሆኖ ቀርቦ፡-			
3.1	በአንድ ጊዜ አጠቃሎ ከከፈለ	70	60	50
3.2	ቢሮው በሚሰጠው እስከ 6 ወራት በሚደርስ የክፍያ ስምምነት ጊዜ ከከፈለ	60	50	40
3.3.	ቢሮው በሚሰጠው ከ6 ወራት በላይ በሆነ የክፍያ ስምምነት ጊዜ ከከፈለ	50	40	30

4	**ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ታክስ ባለመክፈሉ ሀብቱ ከተያዘ በኋላ ሀራጅ ወይም ጨረታ ማስታወቂያ ሳይወጣ ቀርቦ፡-**			
4.1	በአንድ ጊዜ አጠቃሎ ከከፈለ	60	50	40
4.2	ቢሮው በሚሰጠው እስከ 6 ወራት በሚደርስ የክፍያ ስምምነት ጊዜ ከከፈለ	50	40	30
4.3	ቢሮው በሚሰጠው ከ6 ወራት በላይ በሆነ የክፍያ ስምምነት ጊዜ ከከፈለ	40	30	20
5	**ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ታክስ ባለመክፈሉ ሀብቱ ላይ የሀራጅ ወይም የጨረታ ማስታወቂያ ከወጣ በኋላ ቀርቦ**			
5.1	በአንድ ጊዜ አጠቃሎ ከከፈለ	50	40	30
5.2	ቢሮው በሚሰጠው እስከ 6 ወራት በሚደርስ የክፍያ ስምምነት ጊዜ ከከፈለ	40	30	20
5.3	ቢሮው በሚሰጠው ከ6 ወራት በላይ በሆነ የክፍያ ስምምነት ጊዜ ከከፈለ	30	20	10

8. አስተዳደራዊ ቅጣት ሙሉ በሙሉ የሚነሳበት ሁኔታ

ነ) ከዚህ ቀጥሎ በተገለጹት ምክንያቶች በታክስ ከፋዩ የተጣለ አስተዳደራዊ ቅጣት ሙሉ በሙሉ ሊነሳ ይችላል፡፡

ሀ). ታክስ ከፋዩ የታክስ ግዴታውን በመክፈያ ጊዜው እንዳይከፍል የሚያደርግ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ያገጠመው ከሆነ፤

ለ). የድርጅቱ የንግድ ሥራ ሊቀጥል የማይችል እና የከሰረ(bankrupt) መሆኑ በፍ/ቤት ሲረጋገጥ፤

ሐ). ቢሮው የታክስ ከፋዩን ሒሳብ ከመመርመሩ በፊት ታክስ ከፋዩ ስህተቱን በራሱ ተነሳሽነት ያረመ እንደሆነ እና በተሻሻለው የታክስ ስሌት መሰረት ፍሬ ታክስና ወለድ ከከፈለ ፣

መ). ከንብረቱ 20 በመቶ እና ከዚያ በላይ በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ ምክንያት የወደመበት መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ከሚመለከተው የመንግስት ተቋም ያቀረበ ከሆነ፤

ሠ). ከራሱ ገቢ ላይ ግብር ቀንሶ የሚያስቀር ተቀጣሪ በሥራ ላይ እያለም ሆነ የሥራ ውሉ ሲቋረጥ፤

ረ). ለቅጣቱ ምክንያት የሆነው ቢሮው በፈጠረው የአሰራር ስህተት መሆኑን ከተረጋገጠ፣

ሰ). ከወርሃዊ ማሳወቂያ ጋር በተያያዘ በመክፈያ ጊዜው ግብር ከፋዩ ባንክ ገቢ በሚያደርግበት ጊዜ በወቅቱ ቀርቦ ደረሰኝ ባለመቁረጥ ምክንያት በሲስተም የሚሰላው ቅጣት፣

2) ታክስ ከፋዩ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ወይም በቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል ወይም በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም በፍ/ቤት ውሳኔ መሠረት የተሰጠ የታክስ ማስታወቂያ በ30 ቀናት ውስጥ ፍሬ ታክሱን ፣ወለድ እና በከፍተኛ እና በመካከለኛ ደረጃ ለተመደበ ቅጣት በአንቀጽ 7 በተቀመጠው ሠንጠረዥ ተ/ቁ 1.1. መሠረት ከከፈለ፣ በታክስ ውሳኔው ውስጥ የሚገኝ በዝቅተኛ የቅጣት ደረጃ የተመደበ አስተዳደራዊ ቅጣት ሙሉ በሙ ሊነሳ ይችላል።

9. የቅጣት ይነሳልኝ ጥያቄ አቀራረብ ሥርዓት

1) አስተዳደራዊ ቅጣት የተወሰነበት ሰው ቅጣቱ እንዲነሳለት ምክንያቱን በመግለጽ ለመምሪያ ወይም ለጽ/ቤት ለግብር አወሳሰን አሰባሰብና ክትትል ዋና የሥራ ሂደት ወይም ለጽ/ቤት ኃላፊ በጽሑፍ ማመልከት አለበት።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው ቢኖርም የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት የገባ ሰው ፍሬ ታክሱን ፣ ወለዱንና የማይነሳውን ቅጣት ከፍሎ ከጨረሰ ማመልከቻ ማቅረብ ሳያስፈልግ ቅጣቱ የሚነሳ ይሆናል።

10. ቅጣትን የማንሳት ሥልጣን

1) የመምሪያው ወይም የከተማ ወይም የወረዳ ወይም የክፍለ ከተማ የግብር አወሳሰን አሰባሰብና ክትትል ዋና የሥራ ሂደት አስተባባሪ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 እና 8 መሰረት ቅጣት ያነሳል።

2) አስተዳደራዊ ቅጣት ስለመነሳቱ ለዚህ ዓላማ በተዘጋጀ ቅጽ ተሞልቶ በሥራ ሂደቱ ከተረጋገጠና ከጸደቀ በኋላ የሚከፈለው ታክስ፣ ወለድና የማይነሳው የቅጣት መጠን ተከፍሎ ቀሪው ቅጣት ዕዳውን በሚከታተለው የግብር አወሳሰን፣ አሰባሰብና ክትትል የሥራ ሂደት አስተባባሪ ወይም የእዳ ክትትልና አሰባሰብ ባለሙያ ከሲስተም (SIGTAS) ላይ ተገቢው መግለጫ ሰፍሮ እንዲሰረዝ ይደረጋል።

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የግብር አወሳሰንና አሰባሰብ ክትትል ዋና የሥራ ሂደት አስተባባሪ በሚወስነው የቅጣት አነሳስ ላይ በታክስ ከፋይ የሚቀርብ ቅሬታ በየደረጃው የሚገኘው የደንበኞች አገልግሎት ዋና የሥራ ሂደት ቅሬታውን በመቀበል መርምሮ ለመምሪያው ወይም ለጽ/ቤት ኃላፊ የውሳኔ ሀሳብ በማቅረብ ያስወስናል። በውሳኔው መሠረት ተፈጻሚ ይደረጋል።

11. አስተዳደራዊ ቅጣትን በልዩ ሁኔታ ስለማንሳት

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5፣ 7 እና 8 ላይ የተመለከተው ቢኖርም በኢኮኖሚያዊ፣ አስተዳደራዊ ወይም ማህበራዊ ምክንያቶች የቢሮው ኃላፊው በታክስ ከፋዩ ጥያቄ መሠረት ወይም በቢሮው የራስ ተነሳሽነት መሠረት የተጣለን አስተዳደራዊ ቅጣት በልዩ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሊነሳ ይችላል፡

2) በልዩ ሁኔታ የሚታይ የቅጣት ይነሳልኝ ጥያቄ በመምሪያ ወይም በጽ/ቤት መቅረብ ያለበት ሲሆን መምሪያው ወይም ጽ/ቤቱ ጥያቄውን ከታክስ ከፋዩ የሚፈለግ ጠቅላላ የታክስ ዕዳ መጠን፣ የታክስ ዓይነት፣ የታክስ ዕዳው ያለበት ሁኔታ፣ የታክስ ከፋዩ የታክስ አከፋፈል ታሪክ፣ በልዩ ሁኔታ ቅጣት እንዲነሳ የተጠየቀበትን ተጨባጭ ምክንያትና ማስረጃ፣ እንዲሁም በጉዳዩ ላይ የመምሪያው ወይም የጽ/ቤቱ ዝርዝር የውሳኔ ሀሳብ በመምሪያ ወይም በጽ/ቤት ኃላፊ ተፈርሞ ለቢሮው የግብር አወ/አሰ/ክትትል ዋና የሥራ ሂደት መላክ አለበት፡፡

3) የቢሮው የግብር አወ/አሰ/ክትትል ዋና የሥራ ሂደት ዳይሬክተር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ከመምሪያው ወይም ከጽ/ቤቱ የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ እንዲሁም የግብር ከፋዩን ጥያቄ እና ስለጉዳዩ የቀረበውን ማስረጃ መርምሮ ለቢሮው ኃላፊ ዝርዝር የውሳኔ ሀሳብ በማቅረብ አስተዳደራዊ ቅጣት በልዩ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲነሳ ለውሳኔ ይያቀርባል፡፡

4) ለቢሮው ኃላፊ ቀርቦ በሚወሰነው ውሳኔ መሠረት እንዲፈጸም በግብር አወሳሰን አሰባሰብና ክትትል ዋና የሥራ ሂደት ዳይሬክተር በኩል ለመምሪያው ወይም ለጽ/ቤቱ የሚላክ ሆኖ የሚነሳው አስተዳደራዊ ቅጣት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ተፈጻሚ የሚደረግ ይሆናል፡፡

5) ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም " የቢሮ ኃላፊ " ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ነው፡፡

12. የክፍያ ጊዜ ስምምነት የሚወሰድ ግብር ከፋይ የቅጣት አነሳስ ስለሚፈጸምበት ሥርዓት

1) በክፍያ ጊዜ ስምምነት መመሪያ መሰረት የታክስ ዕዳውን በተራዘመ ጊዜ ለማስከፈል ከግብር ከፋዩ ጋር በሚደረግ የክፍያ ጊዜ ስምምነት ውል ውስጥ ከፍሬ ታክስና ወለድ በተጨማሪ በዚህ መመሪያ መሠረት የማይነሳው ቅጣት (በከፊል ተነስቶ ከፊሉ ሳይነሳ በሚቀርበት ሁኔታ) ብቻ ተጨምሮ ሊነሳ የሚችለው ቅጣት እንዳይካተት ሊደረግ ይችላል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተገለጸው አግባብ ግብር ከፋዩ በስምምነቱ መሰረት ፍሬ ታክሱንና ወለዱን ከፍሎ ማጠናቀቁ ሲረጋገጥ ቅጣቱ እንዲነሳ ይደረጋል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተገለጸው መሰረት ግዴታውን ካልተወጣ ቅጣቱ በቀጣይ ባልተከፈለ የታክስ ዕዳ መጠን መሠረት የሚስተናገድ ይሆናል፡፡

ክፍል ሦስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

13. ወለድ የማይነሳ ስለመሆኑ

1) በክልሉ ገቢ ግብር እና በሌሎች የታክስ አዋጆች መሰረት በዘገየ የታክስ እና የግብር ክፍያ ላይ የሚታሰብ ወለድ በዚህ መመሪያ መሰረት ሊነሳ ወይም ቀሪ የሚደረግ አይሆንም፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በህግ ወለድ መሰላት በሌለበት ሁኔታ በስህተት ተሰልቶ የሚገኝ ወለደ ጉዳዩ በሚመለከተው ባለሙያ መግለጫ እንዲቀርብ ተደርጎ ከሲስተም ላይ እንዲሰረዝ በመምሪያው ወይም በጽ/ቤቱ ኃላፊ ሲወሰን ተገቢው መግለጫ ሰፍሮ ከሲስተም ላይ እንዲሰረዝ ይደረጋል::

14. ሪፖርት ስለማቅረብ

1) በመምሪያው ወይም በጽ/ቤቱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7፣ 8 እና 11 ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲነሱ ውሳኔ የተሰጣቸው አስተዳደራዊ ቅጣቶች የተነሳውን የቅጣት የገንዘብ መጠን በየወሩ ተጠናቅሮ በግልጽ ተለይቶ ከወርሃዊ ሪፖርት ጋር ለቢሮው የገቢ ዕቅድ ግምገማ ጥናት ክትትል የሥራ ሂደት መቅረብ አለበት::

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተመለከተው መሠረት የዞንና የከተማ አስተዳደር ገቢዎች መምሪያዎች ሪፖርታቸውን በየወቅቱ እንዲልኩ የገቢ ዕቅድ ግምገማ ጥናት ክትትል የሥራ ሂደት ክትትል ያደርጋል እንደአስፈላጊነቱ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከተው ዘርፍ ሪፖርት ያደርጋል::

3) ቢሮው አስተዳደራዊ ቅጣት እንዲነሳ ውሳኔ የሰጠበትን የእያንዳንዱን መዝገብ መረጃ ከዞንና ከከተማ አስተዳደር መምሪያዎች በማጠናቀር በየሩብ ዓመቱ ለገንዘብ ቢሮ ሪፖርት ማቅረብ አለበት::

15. የተሻሩና ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች

በሥራ ላይ የነበረው የታክስ አስተዳደር ቅጣት አነሳስ መመሪያ ቁጥር አገቢ 001/2011፣ የታክስ አስተዳደር ቅጣት አነሳስ መመሪያን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር አገቢ 18/2014 እና ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሰርኩላርና ልማዳዊ አሰራሮች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል::

16. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በታክስ አስተዳደር ቅጣት አነሳስ መመሪያ ቁጥር አገቢ 001/2011 መሰረት ተቀባይነት አግኝቶ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዚያ ስምምነት ውስጥ ገብቶ የታክስ ዕዳውን በመክፈል ላይ የሚገኝ ግብር ከፋይ የአስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ ጉዳይ በነባሩ መመሪያ መሠረት ፍጻሜ ያገኛል::

17. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

1) ይህ መመሪያ ከህዳር 1 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል::

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ መመሪያዉ እንደገና አዲስ ቁጥር ከተሰጠበት ቀን በኋላ ያለ መብት ወይም ግዴታ ሕጋዊ ውጤት የሚኖረው

መመሪያው በአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ ተመዝግቦ በገቢዎች ቢሮ ድረ-ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል።

ባህር ዳር ህዳር 1 ቀን 2017 ዓ.ም

ክብረት ማህሙድ ሁሴን

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ